# ወደ ሆስፒታል የሚመጡ ነገሮች

the women's
the royal women's hospital
victoria australia

## ይህ ዝርዝር በሴቶች ሆስፒታል ለሚወልዱ ሴቶች ነው።

### ለምጥ

- ምቾት ያላቸው ልብሶች እንደ አሮጌ ሸሚዝ/t-shirt፤ ሙቀት ያለው ካልሲ፤ አሮጌ ጉርድ የውስጥ ልብሶች (አንዴ የርስዎ ሽንት ውሃ ከፈሰሰ በኋላ አሁንም አሁንም ልብስ መቀየር ሊስፈልግዎት ስለሚችል ብዙ ጥንዶች ያስፈልግዎ ይሆናል)
- የራስዎ ትራስ (አስፈላጊ ከሆነ ምልክት ማድረግ)
- የሞቀ ዝልግልግ ጀል ፓኬት
- ለመታሻ ማዕድን ያለው ዘይት ወይም ሎሽን ቅባት
- በቀዝቃዛ ውሃ ለመርጨት የሚረጭ ጠርሙስ (አሮሶል የሌለበት)
- መጸዳጃዎች፤ ሳሙና፤ ሻምፑ፤ የጥርስ ሳሙና፤ የጥርስ መቦረሻ
- መክሰስ፤ ገብስ ያለበት ስኳር፤ ፈሳሽ ነገር፤ ባቄላ፤ የፍራፍሬ ቁራጭ ወ.ዘ.ተ.
- የቆዳ ማሰሪያ ወይም ነጠላ ጫማ፤ የማያዳልጥ ካልሲዎች
- ካመራ
- የስልክ ቻርጀር
- እርስዎ የሚወዱት ጠቃሚ ዘይት (የዘይት ማሰራጫዎች ይቀርባሉ)
- እርስዎ የሚወዱት ሙዚቃ በ MP 3 መጫወቻ ወይም በስልክ ላይ ሲቀርብ (የድምጽ ማነጋገሪያ ማጉያ አለን)

### ድጋፍ ሰጪ ሰው(ዎች)

- በሚወዱት መክሰስ ላይ የሚካተት፡ ጭማቂ፤ ለየት ያለ ሻሂ፤ አስፈላጊ ከሆነ ለክብረ በአል የሚሆኑ መጠጦች ይሆናል።

### እናትና ልጅ

- ምቾት ያለው ልብሶች፤ ጫማዎች፤ ነጠላ ጫማዎች ወይም የማያንሸራትቱ ካልሲዎች (የእግር ጫማ ካልሲ ሁልጊዜ ማርጀት አለበት)።.
- በማታ የሚለበስ፤ ከፒጃማና ጋዎን ቀሚስ ባሻገር የሌሊት ልብስ ወይም የማታ ሸሚዝ ይሻላል
- የጡት እንክብካቤ መያዣ ወይም ሽቦ የሌለበት ጡት መደገፊይ ልብስ (በአካል እንቅስቃሴ ላይ እንደሚጠቀሙት አይነት) እና የጡት ማጥቢያ መደገፊያ ገንባሌ ያሉት።
- የውስጥ ሱሬ፤ በወገብ-ቁመት በሙሉ ሽፋን (ከሴት ዋና ልብስ ባሻገር) እና ከነዚህ ብዙዎች!
- በወሊድነት የመጠቅለያ ጨርቅ (3 እሽጎች)
- ለህጻን ናፒ/ሽንት ጨርቅ (በገብያ ያልወጣ የህጻን መጥረጊያ) ድቡልቡል ጥጥ እና ታጥቦ የሚጣል ጨርቅ። የበለጠ ምክር ለማግኘት ለልጅዎ ቆዳ እንክብካቤ በሚለው የመረጃ ዝርዝር ወረቀት ላይ ማየት።
- መጥረጊያ ስስ የጥጥ ጨርቅ - የህጻን ሰውነት አጥቦ ወደ ቤት ለመውሰድ
- አዲስ ለተወለደ ናፒስ/ሽንት ጨርቅ (32 እሽጎች)
- የህጻን ልብሶች፡ እጅታ ያላቸው ካኔትራዎች እና ረጅም እጅታ ያላቸው በጣም ጥሩ ናቸው

- ለልጅዎ ሰው ሰራሽ ወተት በመጠቀም ለመገብ የምያቅዱ ከሆነ፤ እባክዎ እርስዎ የመረጡትን ሰው ሰራሽ ወተት በጣሳ ወይም በትንሹ የታሸገን ይዘው መምጣት።
- የህጻን በመኪና ማስቀመጫ (ከሆስፒታል በሚወጡበት ቀን)
- ወደ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ የህጻን ብርድ ልብስ/አንገት።
- እባክዎ ጌጣጌጥ፤ የክረዲት ካርድ እና ሌላ ዋጋ ያላቸውን ከቤት ይዞ አለማምጣት።

ብዙ ጥሬ ገንዘብ አለማምጣት።

### የጉብኝት ሰዓታት

የጉብኝት ሰዓታት ከሰዓት በኋላ 2.30pm እስከ 8.00pm መካከል ብቻ የተወሰነ ነው። የትዳር ጓደኛ ከጥዋቱ 8.00am እስከ 8.30pm ባለው ጊዜ መጎብኘት ይችላል።

### የርስዎ ቆይታ

ልጅዎ ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ከወሊድ በኋላ ማቆያ መኝታ ክፍል ይተላለፉና እንክብካቤና ክትትል ይደረግልዎታል። ስለርስዎ ከሆስፒታል መውጣት ያለን እቅድ የርስዎ አዋላጅ ነርስ ታነጋግርዎታለች። የርስዎ አወላለድ የተወሳሰበ ካልሆነ እና እርስዎና ህጻኑ ደህና ከሆናችሁ በወለዱ በ24 ሰዓታት ውስጥ ከሆስፒታል ይወጣሉ። እርስዎ በ24 ሰዓታት የመውጫ መተላለፊያ መንገድ ከሆኑ ብዙጊዜ እርስዎን ለመርዳትና ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ለማወቅ ባለቤትዎ ለሊቱን ከርስዎ ጋር መቆየት ይችላል።

በቀዶ ጥገና ወልደው ከሆነ እና በርስዎና ልጅዎ ላይ ሁሉም ነገር በደህና እየተካሄደ ከሆነ ከወለዱ በኋላ ሆስፒታል የሚቆዩት እስከ 72 ሰዓታት ይሆናል። ብዙ የተወሳሰበ ወሊድ ወይም ህጻን ላጋጠማቸው ሴቶች እና ደህና ካልሆኑ በሆስፒታል ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያሉ።

**ከመኝታ ክፍል የመውጫ ሰዓት ጥዋት 9.30am ነው።**

እባክዎ በተቻለ መጠን በዚህ ጊዜ ወደ አቅራቢያ ለሚወስድዎ ማቀናጀት።

ያስተውሉ፡ በራስዎ መኪና ወደ ቤት የሚሄዱ ከሆነ የርስዎ ህጻን ከመወለዱ በፊት ትክክለኛ የሆነ የህጻን ማሰሪያ መግጠም ያስፈልጋል። (በVicRoads ድህረገጽ website www.vicroads.vic.gov.au ላይ ማየት ወይም ለቪክሮድስ/VicRoads ህጻን ማሰሪያ ጥራዝ ወረቀት እንዲሰጥዎ አዋልጅ ነርስ መጠየቅ)።

### ለበለጠ መረጃ

የታካሚዎች እና ጎብኝዎች ክፍል በሚለው የእኛ ድህረገጽ ላይ ማየት www.thewomens.org.au/PatientsandVisitors

**በተዛማጅ የመረጃ ዝርዝር ወረቀት**

ለልጅዎ የቆዳ እንክብካቤ

**የክህደት ቃል** ይህ የመረጃ ዝርዝር ወረቀት ለአጠቃላይ መረጃ ብቻ ተብሎ የቀረበ ነው። ስለልጅዎ እና የርስዎ ጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ለየት ያለ ምክር ለማግኘት ከርስዎ የጤና ባለሙያ ምክር ማግኘት አለቦት። በዚህ የመረጃ ዝርዝር ወረቀት ላይ ተመርኩዞ ለሚ ከሰት ማንኛውም ጥፋት ወይም ለሚነሳ ጉዳት በሮያል ሴቶች ሆስፒታል በኩል ተቀባይነት አይኖረውም። ለእርስዎ ወይም ለህልጅዎት በአስቸኳይ ህክምና እንዲደረግልዎት ከፈለጉ፤ እባክዎ በአቅራቢያዎ ያለን የድንገተኛ ህክምና ክፍል ያነጋግሩ።
© The Royal Women's Hospital 2018